# ጀርመን አገር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንና የግብጽ ኮፕቲክ ቤተክርስቲያን የጋራ ሲኖዶስ አቋቋሙ!




***Neue Westfälische Zeitung von 21. August 2015 Höxter***

**Vertragsunterzeicnung im Koptenkloster:** ***Erzbischof Moussa (2. v. l.) und Bischof Anba Damian (Mitte) setzen ihre Unter- schriften unter den Vertrag. Mit dabei waren Pater David Moussa aus Ägypten sowie die Kloster-Besucher Monsignore Peter von Steinitz (l.) und Diakon Christoph Prinz zu Bentheim (r.) sowie Mizan Ghibru (im Hintergrund, v.l.), Magdalene Girma, Sara Kidani und Modes Teschomi von der Äthiopisch-Orthodoxen Kirche.***

■ **Brenkhausen** (mbr). Die orientalisch-orthodoxen Kirchen in Deutschland wollen eine gemeinsame Synode gründen. Den Anfang machten gestern die Koptisch-Orthodoxe Kirche und die Äthiopisch-Orthodoxe Kirche. Im Koptenkloster in Brenkhausen unterzeichneten Bischof Anba Damian (koptisch-orthodox) und Erzbischof Moussa (äthiopischorthodox) einen entsprechenden Vertrag. Bischof Damian ist der Initiator der Synodengründung. Denn die Koptisch-Orthodoxe Kirche strebt die Anerkennung als Körperschaft des öffentlichen Rechts an. Bislang ist die Kirche ein gemeinnütziger Verein, erklärte Bischof Anba Damian. Die Anerkennung als Körperschaft des öffentlichen Rechts scheiterte bislang an der zu geringen Mitgliederzahl, die mindestens ein Promille der Bevölkerung betragen muss. In Deutschland leben aber nur 12.000 Kopten. Zusammen mit der Äthiopisch-Orthodoxen Kirche, die mehr als 100.000 Mitglieder in Deutschland hat, schafft man nun den Sprung über die „Ein-Promille- Hürde". „Als Körperschaft des öffentlichen Rechts haben wir eine Vielzahl von Vorteilen. Unter anderem können wir Entwicklungshilfeprojekte für unser Heimatland Ägypten selbst in die Hand nehmen." Bislang mussten die Kopten dabei die Hilfe der Evangelischen oder der Katholischen Kirche in Anspruch nehmen. Geplant ist, dass auch die Armenisch-Apostolische Kirche, die Indisch-Orthodoxe Kirche, die Eritreisch-Orthodoxe Kirche und die Syrisch-Orthodoxe Kirche der Synode beitreten.

## የጋዜጣው ይዘት ትረጉም፤

**የአዲሲቱ ዌስትፋሊያ ጋዜጣ ነሃሴ 21 ቀን 2015 - ሆከስተር**

**በኮፕት ገዳም የውል ሰነድ ፊርማ፤** ሊቀጳጳስ ሙሴ (2. ከገራ ወደቀኝ) እና ጳጳስ አንባ ዳሚያን (የመካከለኛው ) (ከመሃል) ፊረማቸውን በውሉ ሰነድ ላይ አስቀመጡ። በዚሁ ጊዜ በቦታው የነበሩ፤ አባ ዳዊት ሙሳ ከግብጽ እንዲሁም የገዳሙ ጎብኝ እንግዶች /ካቶሊኮች/ ሞሲኞር ፔተር ፎን ሽታይኒትጽ (ከግራ) እና ዲያቆን ክርስቶፍ ፐሪንስ ቤተልሄም (ከቀኝ) እንዲሁም ሚዛን ገብሩ (ሁዋላ ከግራ) ማግዳሌና ግርማ፤ ሳራ ኪዳኔ እና ሞገስ ተሾመ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን.

■ **ብሬንከሃውዘን (መቢአር)።** በጀርመን የኦርየንታል ((የመካከለኛው ምስራቅ)) ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያናት አንድ የጋራ ሲኖዶስ ለመመስረት ስለፈለጉ፤ ትላንት የኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የመጀመሪያውን እርምጃ ወስደዋል። በዚህም መሰረት ጳጳስ አንባ ዳሚያን (የኮፕት ኦርቶዶክስ) እና ሊቀጳጳስ ሙሴ (የኢትዮጵያ ኦረቶዶክስ) ውል ተፈራርመዋል። የዚህን የጋራ ሲኖዶስ መመስረትን ሃሳብ አመንጪም ጳጳስ አንባ ዳሚና ሲሆኑ፤ ጥረታቸውም እስካሁን Gmemeinnütziger Verein (ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት) በሚል የሚታወቀው ቤተክርስተያናቸው፤ Körperschaft des Öffentlichen Rechts (Corporation of public law) በሚል እንዲታወቅ ለማድረግ ሲሆን፤ ይህ እስከዛሬም ሊሆን ያልቻለበት ምክንያት፤ በጀርመን የሚገኙ የኮፕቲክ ተከታዮች ቁጥር በጣም አነስተኛ በመሆኑ ነበር፤ ይህ ቁጥር ቢያንስ ከሃገሪቱ ነዋሪ ሕዝብ አንድ Promille (per mille) የሚሆነውን መወከል ስለሚገባው፤ በጀርመን ውስጥ የሚኖሩት ኮፕቲኮች ግን 12000 ብቻ ናቸው። ይህ ቁጥር በጀርመን ከ100 000 በላይ አባል ካለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ጋር በጋራ ሲጠቃለል የአንድ Promille የሚሆነውን ገደብ ማለፍ ይችላል። ብሎም ይህ የተቋቋመው የጋራ ሲኖዶስ እንደ Corporation of Public law ሲታወቅ ብዙ ጥቅሞች ይኖሩናል፡፡ ከነዚህም መሃከል ለእናት ሃገራችን ግብጽ የልማት ሮጀክቶችን በራሳችን እጅ ማስገባት እንችላለን። እስካሁን ድረስ ግን ኮፕቶች የወንጌላውያንን ቤተክርስቲያን ወይም የካቶሊክ ቤተክርስቲያንን እርዳታ መጠበቅ ይገባቸዋል። ወደፊት የአርመን አፖስትል ቤተክርስቲያን፤ የህንድ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን፤ የኤርትራ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እና የሲሪያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የጋራ ሲኖዶሱን እንደሚቀላቀሉም እቅድ አለ።

## አስተያየት

የሁለቱ ቤተክርስቲያናት የጋራ ሲኖዶስ ሲቋቋም ነበሩ ተብለው የተጠቀሱት ሰዎች ገዳሙን በመጎብኘት ላይ የነበሩ እንግዶች ማለትም በአጋጣሚ በቦታው የተገኙ እንጂ በሲኖዶሱ ምስረታ ላይ እንዲገኙ የተጋበዙ ወይም በሌላ ከሲኖዶሱ ምስረታ ጋር ግንኙነት ያላቸው እንዳልነበሩ መገንዘብ ስለሚቻል፤ ከዚያም በላይ በጀርመን ከ12 በላይ የሚሆኑ አድባራትና የነዚሁ አድባራት ካህናትና አለቆች፤ ከዚያም በላይ ቤተክርስቲያኒቱን ላለፉት 30 ዓመታት በበላይነት ሲመሩ የቆዩት ሊቀ ካህን የሚገኙ ሲሆን፤ ከነዚህ አንዳቸውም እንኳን በዚህ የሲኖዶስ ምስረታ ላይ አለመገኘት አጠቃላይ ሂደቱ ጤናማ ነበር ብሎ ለማሰብ በጣም አስቸጋሪ እንደሚሆን ግልጽ ነው። ባጭሩ በጣም ቅጥ ያጣ አልባሌ ሂደት እንደነበር እንድናስምርበት እንገደዳለን። ይህንን ግን በዚሁ እናቆየውና በእጅጉ ቀልብን ወደሚስበው የሲኖዶሱ መቋቋም መክንያትና ለምንስ አገልግሎት እንደታጨ የሚመለከለተውን ሃሳብ እንመርምር፤

ጋዜጣው እንዳሰፈረው የሲኖዶሱን የማቋቋም ሃሳብ አመንጭ አንባ ዳሚያን እንደሚሉት፤ በጀርመን የምትገኘው የግብጽ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያንን አሁን ከምትገኝበት ለትርፍ የማይሰራ ማህበር ከሚባለው የማህበር ደረጃ ወደሌላ ከፍተኛ ደረጃ አምጥቶ፤ ዛሬ አንዳንድ ለእናት አገራቸው ግብጽ የሚበጁ ልማታዊ እንቅስቃሴዎችን ለማድርግ፤ በጀርመን ያሉትን ሁለት ታላላቅ ቤተክርስቲያናትን ማለትም የጀርመን ወንጌላዊትንና የጀርመን ካቶሊክ ቤተክርስቲያንን ድጋፍ በማግኘት ላይ ተማማኝ መሆንን ማስወገድና የራስን ጉዳይ በራስ ባለቤትነት ለመተካት የሚለውን ህልማቸውን ለማሳካት ማለፍ የነበረባቸውን እንቅፋት ያስወግዳል በማለት የመቱት መላ እንደሆነ ነው።

ይህንን በደረጃው ከፍ ያለ ተቋም ለማደራጀት ጠቀም ያለ የሰው ቁጥር አስፈላጊ የሆነውን ያሕል ታዲያ፤ በጀርመን አገር የሚገኙ የግብጽ ኮፕቲክ ቤተክርስቲያን ተከታዮች ከ12000 ያላለፉ በመሆኑ፤ እስከዛሬ የተፈለገውን ውጤት ለማስገኘት ሳይቻል ቢቀርም፤ ይህንን ቁጥር እንዴት አድርጎ ከፍ ማድረግ እንደሚቻል የማውጣት የማውረዱ ሂደት አልተቋረጠም። ብሎም በመጨረሻ በጀርመን አገር የሚኖሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ተከታዮች ለዚህ የአንባ ዳሚያን ፕሮጅክት ማስፈጸሚያ ይሆኑ ዘንድ የጳጳሱ ዓይን ያርፍባቸዋል። አንባ ዳሚያን የነዚህን የእግዚአብሄር በጎች እረኛ ሲያፈላልጉ ቆይተው፤ መቀመጫቸው ጀርመን የሆነውን ሊቀ ጳጳስ ሙሴን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲ...... ሊቀጳጳስን ያገኙሉ፤ የዚህ ጊዜ ነው እንግዲህ የጋራ ሲኖዶስ ማቋቋም ሃሳብ የመነጨው። አባ ሙሴም 100 000 በጀርመን የሚገኙ የመንፈስ ልጆቻቸውን አንባ ዳሚያን ላቀዱት የጋራ ሲኖዶስ ምስረታ እንዲያገለግል ባርከውና ቀድሰው ያስመዘግባሉ ማለት ነው። የነዚህ የመቶ ሺህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ተከታዮች ዋና ሚናም 12000ው የግብጽ ኮፕቲክ ቤተክርስቲያን ተከታዮች መናጀ በመሆን ቁጥርን ከፍ ማድረግ እንደሆነ እንረዳለን። በመቶው ሺ ቁጥር ጉዳይ ትንሽ ልቆይበት ተገድጃለሁ፤

ለመሆኑ በጀርመን አገር 100 000 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ተከታዮች አሉ? ከሰማንያዎቹ ዓመታት በሰፊው የኢትዮጵያውያን ወደ ጀርመን መፍለስ ጅማሮ ጊዜ አንስቶ፤ እስከዛሬ በዚሁ ሃገር የቆየሁ እንደመሆኔ፤ ከሞላ ጎደል ስለጉዳዩ ካለኝ ዕውቀት ስነሳ፤ ዕውነት ዕውነት እላችኋለሁ፤ ባሁኑ ጊዜ ኢትዮያዊ፤ ትውልደ ኢትዮጵያዊ፤ በጀርመን ተወልዶ ያደገው፤ ሁሉ አንድ ላይ ተሰባስቦ ቢሰላ ከ30 ወይም እጅግ ቢበዛ ከ40 ሺ አይበልጥም። ይህም ቁጥር እስከዚህ ሊደርስ የሚችለው ኤርትራ ነጻ ከመውጣቷ በፊት ባለው ጊዜ ኤርትራውያንም እንደ ኢትዮጵያ ዜጋ ስለሚቆጠሩ እነሱንም የሚጨምር ሲሆን፤ ዛሬ ግን እነሱ በሌላ መዝገብ ስለሚያዙ የኢትዮጵያው ቁጥር ከ20ው ወይም ከ30ው ሺ የሚያልፍ አይሆንም። ከዚህ ውስጥ ምናልባት በርከት ያለ ቁጥር የሚኖረው የኦርቶከዶክስ ቤተክርስቲያን ተከታይ መሆኑ ብዙም ላያከራክር ይችል ይሆናል፤

ብሎም እንግዲህ፤ ለግብጽ ኮፕቲክ ቤተክርስቲያን ምኞት ማሚያ የሚሆን በውሸት የተቀናበረ ቁጥር በመፈብረክ፤ ከዛሬ 55 ዓመት በፊት የራሷን ፓትርያሪክ በመሾም ከግብጽ ኮፕቲክ ቤተክርስቲያን ሞግዚትነት ነጻ የወጣችውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን መልሶ ባሪያ ለማድረግ ለተቀየሰ አሳፋሪ ተግባር የቤተክርስቲያኗን ልጆች ብዛት መጠቀሚያ አድርጎ ማቅርብ ትውልድ የማይረሳው በደል ሆኖ ይመዘገባል። የቁጥር ፍብረካው በሰማይ የሚያመጣውን መዘዝ መናገር ከአቅማችን በላይ ቢሆንም እንኳን በምድራዊው ሕግ ለከፍተኛ ቅጣት የሚዳርግ ወንጀል መሆኑን እንኳ ለመንገንዘብ አለመቻል፤ አጠቃላይ ሁኔታው ምን ያህል ሃላፊነት የጎደለውና አሳዛኝ ድርጊት ብሎ ከመደምደም በላፈ ምን ማለት ይቻላል?

ታዲያ ይህ አሰፋሪ ድረጊት እንዲሁ በቀላሉ የአንድ ምስኪን ሊቀጳጳስ ድርጊት ነው ብሎ ማለፍ ደግሞ በራሱ ጥፋት ስለሚሆን የዛሬዋ ኢትዮጵያ የምትገኝበትንም ሁነታ ዞር ብሎ ተመልክቶ ሂደቱን በውል ማየት ያስፈልጋል። በትግራይ ሕዝብ ነጻነት ግንባር የሚዘወረው ዘረኛ ስረዓት ኢትዮጵያን በማፈራረስ ፐላኑ ውስጥ ከተሰማራባቸው የጥፋት መስኮች አንዱ በሃይማኖት ውስጥ ጣልቃ በመግባት ትርምስ መፍጠርን ስለሆነ፤ በዚህም አሁን በጀርመን የተፈጸመውን የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን የሚያዋርድ ስራ እንዲፈጸም በማድረጉ የወያኔ እጅ የለበትም ማለት እራስን ማጃጃል ከመሆን የሚያልፍ አይሆንም። የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ኢትዮጵያውያን ድምጻችን ይሰማ ብለው ሲጮሁ፤ ለምንድነው ኦርቶዶክሱ በሰላማዊ ሰልፍ ወጥቶ የማይቃወማቸው ብሎ በአደባባይ ሲናገር፤ እንዲደርስ የሚፈልገውን የእሳት ቃጠሎ አስቦ መሆኑን እንደማንጠራጠረው ሁሉ፤ በዚህ አባ ሙሴ በፈጸሙት አሳፋሪ ተግባርም ወያኔ እጁ እንደሌለበት ለመጠርጠር አይዳዳንም። „ጌታዋን የተማመነች በግ ላቷን እደጅ አድርጋ ታድረለች“ እንደሚባለው በወያኔው አጋፋሪነት ብቻ ሳይሆን አስገዳጅነትም ጭምር የተሾሙት ፓትርያሪክ - የአዲስ አበባው አባ ማትያስ የጀርመኑ የጋራ ሲኖዶስ ሲያቋቋም ከአባ ሙሴ ጀርባ ባይኖሩ እኮ! ... ብለን ብንጠረጥረስ? ልብ በሉ እሰከ ዛሬ ሕጋዊው ሲኖዶስና ኢ-ሕጋዊው ሲኖዶስ ወይም የሃገር ቤቱና የውጩ እያልን በምንጠራው ላይ የጀርመኑ የጋራ ሲኖዶስ እያልን ሶስት ሲኖዶሶች ልናስተናግድ ነው ማለት ነው።

በጀርመን የምንገኝ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ልጆች ይህንን በኛ ስም የተፈጸመ አሳፋሪ ተግባር መቀልበስ ግዴታችን መሆኑን አምንንና ተቀብለን በሕብረት ባስቸኳይ መነሳት አለብን።

ዓለሙ አምላኩ

a.amlaku@yahoo.com